EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 5

## ባህል

PK3



AppleTree

EVERY CHILD READY @Home

# Unit 5

## Culture

AppleTree

©2020
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከዚህ በታች በቅጂ መብት የተያዙትን መብቶች ሳይገድብ ፣ የትኛውም የዚህ ህትመት ክፍል  እንደገና ሊባዛ ፣ ሊከማች ወይም ወደ ሌላ የማስመለሻ ስርዓት ሊተላለፍ አይችልም  ፣ ወይም በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ ፣ ሜካኒካል ፣  ፎቶ ኮፒ ማድረግ ፣ መቅዳት ወይም በሌላ መንገድ) ያለ ቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ።

AppleTree Institute for Education Innovation
1801 Mississippi Ave SE, 3rd Floor
Washington, DC 20020

የቅጂ መብት © 2020 ጽሑፍ እና ስዕሎች። AppleTree Institute(አፕል ትሪ ኢንስቲትዩት) መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# PK3 ክፍል 5 ጠቅላላ ምልከታ



## ክፍል 5 ቃላት

- ጥልቅ ሸለቆ
- ልብስ
- ባህል
- አፈ ታሪክ
- የተሸመነ ልብስ
- ማንዳላ
- ፓስፖርት
- ቃል

ውድ ቤተሰቦች፡

ወደ ክፍል 5 እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 5 ስር ልጅዎ ስለ ባህል በተመለከተ ይማራል። ምንም እንኳ ባህሎች አንድ አይነት ባይሆኑም ሙሉ በሙሉ ግን አይለያዩም። ልጅዎ ስለ ባህሎች አምስት ባህሪያት ማለትም፡ ምግብ፣ ቋንቋ፣ ክብረ በአላት፣ አልባሳት እና ሥነ ጥበብ/አርት ይማራል።

## የክፍል 5 መጻህፍት




- *አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/Alex Learns to Play* በ Lindsey Johnson
- *ጥልቅ ሸለቆ/The Canyon* በ Felicia R. Truong
- *በዓለም ዙሪያ ያደረኩት ጉዞ /My Road Trip Around the World* በ Felicia R. Truong
- *የሶፊ የአትክልት ቦታ /Sophie's Garden* በ Felicia R. Truong

***የECR @ Home Activities ከሌሎች ጋር ግንኙነት ስለማድረግ እና ለሌሎች ሰዎች ክብር ስለመስጠት፣ እስከ 7 ድረስ መቁጠርን፣ መመሪያዎችን መከተልን፣ ጥንድ ቃላትን መስራትን እና የድምጽ ቀለሞችን ቃል ለመፍጠር መቀላቀልን ይይዛሉ። ህጻናት በተጨማሪም በምግብ ላይ አንዳንድ ሙከራዎችን ይሰራሉ እንዲሁም ስለ ስሜት ህዋሳት ይወያያሉ። ህጻናት ስለተለያዩ ባህሎች እና የየራሳቸውን ባህሎች ስለማክበር ይማራሉ።***


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 1


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ጠቅላላ ምልከታ

## ባህል ምንድን ነው?

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ:

ስለ ባህል አምስት ባህሪያት ማለትም: ምግብ፣ ቋንቋ፣ ክብረ በአላት፣ አልባሳት እና ሥነ ጥበብ/አርት ይማራል። ልጅዎ በተጨማሪም ስለራሱ ባህል ይማራል። በመጨረሻም ልጅዎ በታሪኮች ውስጥ ስለሚገኙ ዋና ዋና ገጸ ባህሪያት፣ መመሪያዎችን ስለመከተል፣ ቁሶችን ስለመለየት፣ የቃላት የድምጽ ቀለሞችን ስለመቀላቀል እና ጥንድ ቃላትን ስለመመስረት ይማራል።



### ቁልፍ ቃላት



## ባህል

በተወሰነ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የሚጋሩትና ተቀባይነት ያገኘ እምነቶች፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ሥነ ጥበብ/አርት እና ልማዶች ነው።



## ማንዳላ

የአርት ጂኦሜትሪያዊ ክበቦች


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

## አስቡበት!

በዚህ ሳምንት ሰዎች እንዴት በጥቂቱ እንደሚለያዩ ሆኖም በአብዛኛው ተመሳሳይ እንደሆኑ በተመለከተ ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት እርስዎን ልዩ ስለሚያደርግዎ የሆነ ነገር ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 1

## **STEM:** ቁሶችን መለየት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: እንደ ቅጠሎችና ቁጥቋጦዎች፣ ኩባያዎችና ሳህኖች ያሉ ውስጣዊና ውጫዊ ቁሶች (የእያንዳንዱ አይነት ቢያንስ 2)**

- ለልጅዎ **እስኪ እነዚህን ቁሶች እንለይ እና ተመሳሳይ የሆኑትን አንድ ላይ እናስቀምጣቸው** ብለው ይንገሩት።
- **በአንድ ቡድን በውስጥ እና በሌላ ቡድን በውጭ የምናገኛቸውን ቁሶች እየፈለግን ቁሶቹን እንለይ እና መድበን እናስቀምጣቸው** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን ቁሶችን አንድ ላይ እንዲያስቀምጥ ያድርጉ። ልጅዎ ቁሶቹን ለይቶ ስለሚያስቀምጥበት ሌላ ዘዴ ሊያስብ ይችላል።

## በግል መማር: ስለ ባህል ማስተዋወቅ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **በመቀጠል ስለ ባህል እንማራለን። ተመሳሳይ ባህል ያላቸው ሰዎች እንደ ቋንቋ፣ ምግብ፣ አርት፣ አለባበስ እና ክብረ በአላት የመሳሰሉ ነገሮችን ይጋራሉ። በአለማችን ላይ በጣም ብዙ የተለያዩ ባህሎች አሉ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር ስለ ባህላችሁ በተመለከተ ይነጋገሩ።
- ልጅዎን ባህላችሁን ልዩ ስለሚያደርገው ነገር እራሱን ችሎ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለጻፍካቸው እና ስለሳልካቸው ባህላችንን ልዩ ስለሚያደርጉት አንዳንድ ነገሮች ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 1

## ማንበብና መጻፍ: ተራ መመሪያዎች

- ለልጅዎ **እንድትከተል የምፈልገው አንድ ተራ መመሪያ እሰጥሀለሁ። በጥሞና አዳምጠኝ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ተራ ባለ አንድ ደረጃ መመሪያ ይስጡት: የሞኝ ፊት አሳይ፣ በሞኝ ድምጽ ሰላምታ ስጥ፣ አዝናኝ ድምጽ አውጣ፣ ወዘተ
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያዎችን መስጠት እንዲችል ሚናዎቻችሁን ተቀያየሩ።

## ያንብቡ: *አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/**Alex Learns to Play***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *[አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/Alex Learns to Play]*




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/Alex Learns to Play* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም **እየተጫወትክ ቢሆን ኖሮ እና አሌክስ ጨዋታህን ሊቀላቀል እንደሚፈልግ ብታይ ኖሮ ለአሌክስ ምን ትለው ነበር?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 2

## STEM: የበሰለ እና ያልበሰለ ምግብን ማነጻጸር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የአንድ ምግብ የበሰለ እና ያልበሰለ አይነት፡ ምሳ፡ የበሰለና ያልበሰለ ፓስታ፣ ሩዝ፣ ባቄላ፣ ወዘተ**

- ለልጅዎ **ምግብ በባህሎች ውስጥ አስፈላጊ ነው። አብዛኞቹ ምግቦች እኛ እንድንመገባቸው መብሰል አለባቸው። እስኪ በበሰለ ፓስታ እና ባልበሰለ ፓስታ መካከል ያለውን ልዩነት እናነጻጽር** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር በምግቡ ላይ ስላለው ልዩነት ይነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰጥ፣ ምን አይነት ጣዕሞች እንደሚሰጥ (ያልበሰለውን ምግብ መቅመስ ችግር የማይፈጥር ከሆነ)፣ ምን እንደሚመስል፣ ወዘተ።
- ልጅዎን ምግብ ሲበስል እና ሳይበስል ምን እንደሚመስል እንዲስል ያድርጉ።.

## በግል መማር፡ የሙዚቃ መሳሪያ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ባዶ የጫማ ሳጥን ወይም ትንሽ ሳጥን (ሊድ የሌለው) እና የጎማ ማሰሪያዎች ወይም የፕላስቲክ ጠርሙስ ከትናንሽ ጠጠሮች ወይም ያልበሰለ ሩዝ ጋር፣** ***በአማራጭነት - ቀለም***

- ለልጅዎ **የራስህን የሙዚቃ መሳሪያ መስራትና የተለያዩ ባህሎች ሙዚቃዎችን መጫወት ትችላለህ** ብለው የንገሩት።
- ልጅዎ ምን እንደሚደርግ ከተረዳ በኋላ ልጅዎን የጎማ ማሰሪያዎችን በሳጠኑ ዙሪያ በማሰር ጊታር እንዲሰራ ወይም ትናንሽ ጠጠሮቹን ወይም የሩዝ ፍሬዎችን ጠርሙሱ ውስጥ በመጨመር መበጥበጫ እንዲሰራ ያድርጉ። ልጅዎ በተጨማሪም የሙዚቃ መሳሪያውን ቀለም ሊቀባ ይችላል።
- ከዚያም ለልጅዎ የሙዚቃ መሳሪያውን በሚጫወትበት ወቅት ለመጫወት የሚፈልገውን ሙዚቃ እንዲመርጥ ይፍቀዱለት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 2

## ማንበብና መጻፍ: ጥንድ ቃላትን መመስረት



አስፈላጊ ቁሳቁሶች: የተቆራረጡ ጥንድ ቃላት 2

- ለልጅዎ **አሁን ስለ ጥንድ ቃላት እንማራለን። ጥንድ ቃል አሳይህ እና የትኞቹ ቃላት ይህን ቃል እንደፈጠሩ ትፈልጋለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ የ"pancake" የስረኞቹን የሚገጣጠሙ ክፍሎች ያሳዩት። ከዚያም **ይህ pancake ነው። አሁን እስኪ pancakeን የመሰረቱ ሁለት ቃላትን እንፈልግ። pan ይበሉና እስኪ panን እንፈልግ** ብለው ይንገሩት። መጥበሻውን ከኬኩ ስዕል በታች ያስቀምጡት።
- **ከ pancake መጨረሻ የምትሰማው የትኛውን ድምጽ ነው? Pan** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **cake። ጥሩ ሰርተሀል cake ነው። እስኪ ኬኩን እንፈልግ** ብለው ይንገሩት። ለልጅዎ መልሱን ቢነግሩትም ምንም ማለት አይደለም፣ ልጅዎን ለሙከራው ያሞግሱት። **ኬኩን ከመጥበሻው ጎን ያስቀምጡ።**
- ለልጅዎ ስዕሎች ያሳዩት። **ከዚያም እስኪ ቃላቱን አንድ ላይ ሆነን pan** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **cake፣ pancake ብለን እንጥራቸው!** ብለው ይንገሩት።
- በሚከተሉት ቃላት ደግመው ይስሩ: housefly እና strawberries። ልጅዎን ጥንድ ቃሉን የመሰረቱትን ቃላት ፈልጎ እንዲያገኝ ያበረታቱት። ለልጅዎ ስዕሎቹን ቢያሳዩትም ምንም አይደለም፣ ገና በመማር ላይ ስለሆነ።
- ስዕሎቹን ለቀጣዩ ሳምንት ስራ ያስቀምጧቸው።

## የጆርናል ሙከራ: መጫወት እወዳለሁ/ I Like to Play


ስም: ___________

ስትጫወቱ ምን ማድረግ ትወዳላችሁ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ የመጫወት እወዳለሁ/ I Like to Play የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በሚጫወትበት ወቅት ምን ማድረግ ደስ እንደሚለው ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ በሚጫወትበት ወቅት ምን ማድረግ ደስ እንደሚለው እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ በምትጫወትበት ወቅት ምን ማድረግ ደስ እንደሚልህ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ኬክ



ፓን



ፓንኬክ



ቤሪስ



ስትሮው



ስትሮውቤሪስ


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ሃውስ



ፍላይ



ሃውስፍላይ



ሳንድ



ቦክስ



ሳንድቦክስ


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ቦይ



ካው



ካውቦይ



ቦክስ



ሹ



ሹቦክስ


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ________________

ስትጫወቱ ምን ማድረግ ትወዳላችሁ?


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 3

## **STEM:** እስኪ ለይተን እናስቀምጥ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከ 2-3 የተለያዩ ቀለሞች ያሏቸው ቁሶች (ከእያንዳንዱ ቢያንስ 2)**

- ልጅዎን **እነዚህን ነገሮች እንዴት ለይተን ማስቀመጥ እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት።
- **አዎ፡ እስኪ በቀለማቸው እንለያቸው** ይበሉት። ልጅዎን እንደ አስፈላጊነቱ እየረዱት ቁሶችን እንዲለይ ያድርጉ።
- ቁሶችን የምንለይባቸው ብዙ የተለያዩ መንገዶች አሉ። ልጅዎ ቁሶችን በተለየ መልኩ መለየት ሊፈልግ ይችላል!

## በግል መማር**:** በምወዳቸው ቀለሞች መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [ቅርጾች/Shapes]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የቅርጽ ስዕሎችን ይመልከቱ። ከ3-4 ቅርጾችን በስም ይጥሩና ጎኖቻቸውን ይቁጠሩ።
- ለልጅዎ **ይህ ስኩዌር ነው፣ እስኪ ጎኖቹን እንቁጠር** ብለው ይንገሩት። በሚቆጥሩበት ወቅት በጣትዎ ያመልክቱ**፡፡ 1, 2, 3, 4፡፡ 4 ጎኖች አሉት። አንድ ወደ ታች፣ አንድ የጎን፣ አንድ የቁመት** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ቅርጾችን እንዲስል ያድርጉ። ስዕሎቹ በትክክል ቅርጾቹን ባይመስሉም ምንም ማለት አይደለም። ገና በመለማመድ ላይ ነው!




© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 3

## ማንበብና መጻፍ፡ የቃላት ድምጽ ቀለሞችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **የቃላት የድምጽ ቀለሞች የቃሉ ምቶች ናቸው። እስኪ የውሀን ምቶች እናገናኝ፡ wa-ter** ብለው ይነገሩት።
- ከዚያም **እስኪ የቃላት የድምጽ ቀለሞችን እንቀላቅል! መቀላቀል ማለት አንድ ላይ ማድረግ ነው** ይበሉት።
- **Pop** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **corn። Pop-corn። የቃሉን ክፍሎች አንድ ላይ ያገናኙ። ምን ቃል ይሰማሀል?** ብለው ይጠይቁት።
- ከፍ ያለ ሙገሳ መስጠትዎን አይርሱ! **ጥሩ ስራ ነው!**
- በሚከተሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ: culture (cul-ture) እና building (build-ing)።

## ያንብቡ፡ *አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/**Alex Learns to Play***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/Alex Learns to Play*]()




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/Alex Learns to Play* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም ገጽ 12-13ን ያሳዩት። ቀጥለውም **አሌክስ ከሶፊ ጋር መጫወት ፈልጓል። ከአንድ ሰው ጋር መጫወት ብትፈልግ ምን ልትለው ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ: ቀጥ ብሎ መደነስ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ የተለያዩ ህሎች ሙዚቃዎች**

- ለልጅዎ **እስኪ ቀጥ ብሎ መደነስ እንጫወት። ሙዚቃው በሚጫወትበት ወቅት እኛ እንደንሳለን። ሙዚቃው በሚቆምበት ወቅት ቀጥ እንላለን!** ብለው ይንገሩት።
- ጥቂት ድምጾችን ተጫወቱ እና የተለያዩ አይነት ሙዚቃዎችን ተጫወቱ። ልጅዎ ሙዚቃውን መጫወት እንዲችል ሚናዎቻችሁን ልትቀያየሩ ትችላላችሁ። ልጅዎ የተለዩ ሙዚቃዎችን ሊጫወትና መቼ እንደሚያቆም ሊመርጥ ይችላል።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር: ባሕላችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***በአማራጭነት - እርስዎና ልጅዎ መስራት በምትፈልጉት ነገር ላይ ተመስርቶ***

- ከልጅዎ ጋር ስለ ባህላችሁ እና ከባህላችሁ ውስጥ ስለምትወዱት ልዩ ነገር ይነጋገሩ። ስለምትመገቧቸው ልዩ ምግቦች፣ ስለምታዳምጡት ሙዚቃ፣ ልዩ ክብረ በአላት ወይም ስለ አርት ልትነጋገሩ ትችላላችሁ።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከባህላችሁ ማድረግ ስለምትወዱት ልዩ ነገር ይወስኑ። ለምሳሌ፡ ሙዚቃ ልታዳምጡ፣ ልዩ ምግብ ልትመገቡ፣ ወይም የምትወዱትን የአርት ስራ ልትስሉ/ልትቀቡ ትችላላችሁ።
- ከዚያም አንድ ላይ ሆናችሁ ምን እንዳደረጋችሁ እና ይህ ለምን ለእናንተ ልዩ እንደሆነ ተነጋገሩ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።















© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 4

## **STEM:** የቅመም ዘር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ማንኪያዎች፣ ትሪ ወይም ሳህን፣ እና ከ2-3 የተለያየ ውፍረት ያላቸው የተለያዩ ቅመሞች፣ ምሳ: ማጣፈጫ፣ ሲረፕ፣ ቅባት፣ የአኩሪ አተር ስጎ ወይም የአትክልት ዘይት**

- ለልጅዎ **እስኪ በምግብ ሙከራ እንሰስራ። የትኛው ምግብ በፍጥነት እንደሚደርስ እነናያለን** ብለው ይንገሩት።
- ግብአቶቹን በስም ይጥሩ እና **ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ የሚያጣብቁና ወፍራም ሲሆኑ አንዳንዶቹ አይደሉም። እስኪ የሚያጣብቁት ምግቦች ዘግይተው ወይም በፍጥነት እንደሚደርሱ እንይ** ይበሉት። **ምን ትገምታለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን በትሪው ጫፍ ላይ የእያንዳንዱን ግብአት በጥቂቱ በማስቀመጥ ላይ እንዲረዳዎ ያድርጉ። ከዚያም ልጅዎን ቅመሞቹ ወደ ታች እንዲንሸራተቱ ትሪውን ከፍ እንዲያደርግ ያድርጉ።
- ከዚያም በውጤቶቹ ላይ ተነጋገሩ እና **የሚፈጥኑት እና የሚዘገዩት የትኞቹ ናቸው? ይህ ለምን ሆነ ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር: የአይን ለአይን ግንኙነት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **አንድን ሰው በምናናግርበት ወቅት እያየነው ማናገር አለብን። ይህ እያዳመጥነው እንደሆነ እንዲያውቅ ያስችለዋል** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ አንድን ሰው ስለምታዩባቸው ጊዜያት ይነጋገሩ፤ ምሳ: ሰውየውን በምናነጋግረው ወቅት ወይም ሰውየው የሆነ ነገር እንድናደርግለት ሲጠይቀን። **እራስዎን ከሆነ ሰው ጋር የአይን ለአይን ግንኙነት ሲያደርጉ ሊስሉ ይችላሉ።**
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባባሩን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለሳልከው ስዕል ንገረኝ። አንድን ሰው በምታነጋግርበት ወቅት እያየኸው ማናገር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 4

## ማንበብና መጻፍ: ዋና ገጸ ባህሪ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *[አሌክስ ስለ ጨዋታ ይማራል/Alex Learns to Play]*




- ልጅዎን **እስኪ ስለ ታሪኩ ዋና ገፀ ባህሪ እንነጋገር። በታሪክ ውስጥ ገፀ ባህሪያት ሰዎች ወይም እንስሳት ሊሆኑ ይችላሉ። ዋና ገፀ ባህሪ ታሪኩ በሱ ዙሪያ የሚሰራበት ነው** ብለው ይንገሩት።
- *ለልጅዎ አሌክስ ስለ ጨዋታ ይማራል/ Alex Learns to Playን ያሳዩት።* ***ቀደም ብለን አሌክስ ስለ ጨዋታ ይማራል/ Alex Learns to Play* ምንባብን አንብበናል። የታሪኩ ዋና ገጸ ባህሪ ማን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ገና በመማር ላይ ስለሆነ እርዳታ ቢያደርጉለትም ምንም አይደለም!
- **አዎ፤ አሌክስ ነው። ታሪኩ አሌክስን የተመለከተ ነወው። አሌክስ ዋና ገፀ ባህሪው ነው። እንደ የእድሜ እኩዮቹ ያሉ ሌሎች ገፀ ባህሪያት ያሉ ቢሆንም ታሪኩ ግን ስለ አሌክስ በተመለከተ ነው** ብለው ይንገሩት።
- **እስኪ ስለ አሌክስ እናብራራ። ስለ አሌክስ ምን እናውቃለን?** ብለው ይጠይቁት። ለልጅዎ ታሪኩ ስለ ምን በተመለከተ እንዲያስታውስ ፈጣን የስዕል ምልከታ ሊያደርጉ ይችላሉ። ጥቂት ምሳሌዎች ይስጡት፤ ለምሳሌ: አሌክስ ከጓደኞቹ ጋር መጫወት የሚፈልግ ቢሆንም ለመጠየቅ ያፍራል ወይም ይፈራል። አሌክስ መገንባት ይወዳል፣ ወዘተ

## የጆርናል ሙከራ: ከጓደኞች ጋር መጫወት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ ከጓደኞች ጋር መጫወት/ Playing With Friends የጆርናል ገጽ**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንዴት ከጓደኞቹ ጋር መጫወት እንደሚፈልግ ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ እንዴት ከጓደኞቹ ጋር መጫወት እንደሚፈልግ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ከጓደኞችህ ጋር እንዴት መጫወት እንደምትፈልግ ንገረኝ። ከጓደኞችህ ጋር በምትጫወትበት ወቅት ጥሩ ስሜት የሚፈጥሩልህ ጥቂት ዘዴዎች ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ________________

ከጓደኞቻችሁ ጋር እንዴት መጫወት እንደምትወዱ ጻፉ እንዲሁም በስዕል ሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 5

## STEM: ቅርጹን መፈለግ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ካለፈው ሳምንት በካርዶች የተቆራረጡ ቅርጾች**



- የተለያዩ ቅርጾች ያዘጋጁ እና ለልጅዎ ሌላ የቅርጾች ምድብ ይስጡት።
- **አሁን እኔ የቅርጹን ስም እጠራ እና አንተ ደግሞ ቅርጹን እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ። አራት ማዕዘን!** ብለው ይንገሩት።
- በሌሎች ቅርጾች ደግማችሁ ስሩ። ለልጅዎ ከተለያዩ ቅርጾች መካከል በማሳየት ሊረዱት ቢፈልጉም ምንም ማለት አይደለም።

## በግል መማር: ማንዳላዎች መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ማንዳላዎች/Mandalas፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች፣ *በአማራጭነት - እንደ ማጣበቂያ፣ የደረቁ ባቄላዎች፣ ያልበሰለ ሩዝ፣ ትናንሽ ፓስታ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ማንዳላውን ማስዋቢያ ነገሮች***



- ለልጅዎ የማንዳላዎች ስዕሎች ያሳዩት። ከዚያም **ማንዳላዎች ክቦች የመስራት አርቶች ናቸው። ማንዳላህን በየትኛውም በምትፈልገው መልኩ ማስዋብ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ማንዳላውን ቀለም በመቀባት፣ በማድመቅ እና/ወይም በማጣበቅ እንዲያስውብ ያድርጉ። ልጅዎ በተጨማሪም ምርጫው ከሆነ የራሱን ስሎ ሊያስውብ ይችላል።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ማንዳላህ ንገረኝ። ፓተርኑን ያስዋብከው እንዴት ነበር?** ብለው ይጠይቁት።



© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 1 ቀን 5

## ማንበብና መጻፍ: እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: በቀዳሚው ሳምንት ተቆራርጠው የወጡ** [ጥንድ ቃላት 2]



- ለልጅዎ **እስከ አሁን ስለ ጥንድ ቃላት ስንማር ነበር። እኔ ጥንድ ቃል አሳይህ እና አንተ ደግሞ ቃሉን የመሰረቱትን ቃላት ፈልገህ ታገኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ የሚገጣጠሙ የ"sandbox" ክፍሎችን ያሳዩት። ከዚያም ይህ **sandbox ነው። እስኪ አሁን sandboxን የመሰረቱትን ሁለት ቃላት እንፈልግ። sand ይበሉ። እስኪ sandን እንፈልግ** ብለው ይንገሩት። የ sandbox ስዕልን ከታች ያስቀምጡ።
- **በ sandbox መጨረሻ ላይ የምትሰማው ቃል ምንድን ነው? Sand** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **box**። **ጥሩ ስራ ነው box። እስኪ boxን እንፈልግ** ብለው ይንገሩት። ለልጅዎ መልሱን ቢነግሩትም ምንም አይደለም፤ ለሙከራው ያሞግሱት። **ሳጥኑን ከsandዱ ቀጥለው ያስቀምጡት።**

- ለልጅዎ የጥንድ ቃል ስዕል ያሳዩት። **እስኪ ቃሉን አንድ ላይ እንበል: sand** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **box፣ sandbox!**
- በሚከተሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ: cowboy እና shoebox። ልጅዎን ጥንድ ቃሉን የመሰረቱትን ሁለቱን ቃላት ፈልጎ እንዲያገኝ ያበረታቱት። ልጅዎ ገና በመማር ላይ ስለሆነ ስዕሎቹን ቢያሳዩት ምንም አይደለም!

## ያንብቡ: አሌክስ ስለ ጨዋታ ይማራል/**Alex Learns to Play**

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [*አሌክስ ስለ ጨዋታ ይማራል /Alex Learns to Play*]




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *አሌክስ ስለ መጫወት ይማራል/Alex Learns to Play* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም ገጽ 18-19ን ያሳዩት። ቀጥለውም **ከሌሎች ሰዎች ጋር በምንጫወትበት ወቅት አሌክስና ሶፊ እንዳደረጉት ሁሉ ተራችንን ጠብቀን እንጫወታለን** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር ከጓደኞቻችን ጋር በምንጫወትበት ወቅት ስለምንጠቀማቸው ሌሎች ጥሩ ባህሪያት ይነጋገሩ (ምሳ: ትህትና አዘል ቃላትን መጠቀም፣ ጓደኛችን እንዲያደርግ የምንፈልገውን ነገር ማድረግ ካልፈለገ አለመፈለጉን መቀበል፣ ወዘተ)።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 2


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 5 ሳምንት 2 ጠቅላላ ምልከታ

## አፈ ታሪኮች እና ክብረ በአላት

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ:

The Canyonን በማንበብ ስለ አፈ ታሪኮች ይማራል። ልጅዎ በተጨማሪም ራንጎሊ/ Rangoli, የሚሰራ ሲሆን ይህ የህንድ ክብረ በአል በሆነው ዲዋሊ/ Diwali ወቅት ጥቅም ላይ ይውላል።



### ቁልፍ ቃላት



### ጥልቅ ሸለቆ

በአብዛኛው የወንዝ ወራጅ ውሀ የሚፈስባቸው የሚያሟልጩ ድንጋዮች ያሉበት ጥልቅ ሸለቆ ነው።



### አፈ ታሪክ

በአፍ የሚነገር በአብዛኛው ከወላጆች ወደ ልጆች እየተላለፈ የሚመጣ ታሪክ ነው።



### ዓለም

የምንኖርባት እና ሁሉም ሰዎች፣ ክተሞች እና አገራትን የያዘችው ፕላኔታችን ነች።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

## አስቡበት!

በዚህ ሳምንት ልዩ የታሪክ አይነት ስለሆነው ስለ አፈ ታሪክ ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት የሚወዱትን የታሪክ አይነት ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## STEM: ቅርጾችን መለየት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከሳምንት 1 የተወሰዱ ቅርጾች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በካርዶቹ ላይ የሚገኙትን የተለያዩ ቅርጾች ስሞች ጥሩ።
- የቅርጽ ካርዶቹን በዘፈቀደ ይበታትኗቸው። ከዚያም ልጅዎን **2 ተመሳሳይ ቅርጾችን ፈልግና አንድ ላይ አስቀምጣቸው** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ሌሎች ቅርጾችን እንዲለይ ያድርጉ።
- ቅርጾቹን በዚህ ክፍል ስር ለሚሰሩ ለሌሎች ተግባሮች ያስቀመምጧቸው።



## በግል መማር: የውስጥ እና የውጭ ድምጽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ዛሬ ስለ ድምጻችን በተመለከተ እንነጋገራለን። በምንጫወትበትና ከሌሎች ሰዎች ጋር በምንነጋገርበት ወቅት የውስጥ ድምጻችንን እንጠቀማለን። አንተ የምትቆጣ ከሆነ የእድሜ እኩያህ ከአንተ ጋር መጫወት ላይፈልግ ይችላል** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር የውስጥ ድምጾቻችንን እና የውጭ ድምጾቻችንን መቼ እንደምንጠቀም ይነጋገሩ።
- ወረቀት እኩል ላይ ይጠፉ እና **በወረቀቱ በዚህኛው ክፍል ላይ የውስጥ ድምጻችንን የምንጠቀምበትን ቦታ ሳል። በሌላኛው ጎን ደግሞ የውጭ ድምጽ የምንጠቀምበትን ቦታ ሳል** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ስዕሎችህ ንገረኝ። የውስጥ ድምጽ እና የውጭ ድምጽ የምትጠቀመው የት ነው?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 2 ቀን 6

## ማንበብና መጻፍ፡ መቼት/ቦታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*ጥልቅ ሸለቆ/The Canyon*]



- ለልጅዎ **በታሪክ ውስጥ ስለሚገኙ ገጸ ባህሪያት ወይም አንድ ታሪክ ስለማን እንደሚመለከት ተምረሀል። አሁን ደግሞ እስኪ ስለ ታሪክ መቼት እንማር። መቼት ታሪኩ የሚከናወንበት ቦታ ነው። መቼት ስለ ታሪኮች እንድንረዳ ይረዳናል** ብለው ይንገሩት።
- *The Canyon* ን ያሳዩት። **መቼቱን በስዕሎቹ ላይ እናያለን። በዚህ መጽሀፍ ውስጥ መቼቱ ጥልቅ ሸለቆ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ገጽ 5ን ያሳዩት። **እስኪ ስለ ጥልቅ ሸለቆ መቼት እናብራራ። ምን ይታይሀል? ምን ትመለከታለህ?** ብለው ይጠይቁት።

## ያንብቡ፡ ጥልቅ ሸለቆ/**The Canyon**

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*ጥልቅ ሸለቆ/The Canyon*]




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *The Canyon*ን ያንብቡ።
- ከዚያም **ዋና ዋና ገጸ ባህሪያቱ እነማን ናቸው?** ኮዮቴ እና ጥንቸል።
- **ስለ ኮዮቴ ልትነግረኝ ትችላለህ? ምን ይመስላል? እስኪ ስለ ጥንቸል ንገረኝ። ምን ትመስላለች?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ገጸ ባህሪያቱ ምን እንደሚመስሉ ወይም ምን እንደሚያደርጉ ሊናገር ይችላል።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## STEM: አምስቱ የስሜት ህዋሳት - ምግብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች - ጣፋጭ ምግብ፤ ምሳ: ጣፋጭ ፍራፍሬ፣ እና ኮምጣጣ ምግብ፤ ምሳ: ሎሚ ወይም ብርቱካን**

- ለልጅዎ **ምግብ በባህሎች ውስጥ አስፈላጊ ነው። ምግብ ለመቅመስ በምንሞክርበት ወቅት አምስቱን የስሜት ህዋሳቶቻችንን - መንካት/መዳሰስ፣ መቅመስ፣ ማሽተት፣ መስማት እና ማየትን ልጠቀም እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- **እስኪ ሁለት ምግቦችን በማሽተት፣ በመንካት፣ በመቅመስ፣ በማየት እና በምነንበላበት ወቅት ድምጻቸውን በማዳመጥም ጭምር እንሞክር** ይበሉት። ገለጻ ያድርጉለት።
- ልጅዎ እያንዳንዱን ምግብ ከሞከረ በኋላ ስለ ምግቦቹ የስሜት ህዋሳቶቹን በመጠቀም እንዲገልጽ ያድርጉ። ከዚያም ልጅዎ ጣዕማቸውን (ኮምጣጣ እና ጣፋጭ)፣ ምን እንደሚመስሉ፣ ሽታቸውን፣ ድምጻቸውን እና የሚሰጡትን ስሜት ሊያነጻጽር ይችላል።

## በግል መማር: በከለር መቀባትን በከለር መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ወረቀት፣ [ጥልቅ ሸለቆ]**





- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የጥልቅ ሸለቆዎች ስዕሎችን ይመልከቱ እና ጥልቅ ሸለቆ ጎንና ጎኖቹ ከፍ ያሉ ጥልቅ ጠባብ ሸለቆ እንደሆነና አንዳንዴም በውስጡ ወንዝ ሊፈስ እንደሚችል ያብራሩለት።
- ከዚያም **ዛሬ ጥልቅ ሸለቆ ልትስል ትችላለህ! በዚህ ሳምንት በቀጣይ ስዕልህን በመጫወቻ ሊጥ ጥልቅ ሸለቆ ለመስራት ትጠቀምበታለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ጥልቅ ሸለቆህ ንገረኝ። ጥልቅ ሸለቆህ በውስጡ ወንዝ ይፈሳል?** ብለው ይጠይቁት።
- መቀቢያውን እና የጥልቅ ሸለቆ ስዕሉን በቀጣይ በዚህ ሳምንት ለሚሰራ ተግባር ያስቀምጧቸው።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## ማንበብና መጻፍ፡ እስኪ የቃል የድምጽ ቀለሞችን እንቀላቅል

- ለልጅዎ **እስኪ የቃል የድምጽ ቀለሞችን ቃል ለመፍጠር እንቀላቅል!** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ የአንድ ቃል ሁለት ክፍሎችን እናገራለሁ። አንተ እነዚህን አንድ ላይ አድርገህ ቃሉን ትነግረኛለህ። Puz** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **zle። Puz-zle። ቃሉ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- በሚከተሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ: feeling (feel-ing) እና rabbit (rab-bit)። ልጅዎ እርዳታ ቢየስፈልገውም ምንም ማለት አይደለም። አሁንም ገና እየተማረ ስለሆነ!

## የጆርናል ሙከራ፡ ማታለሎች/ Tricks

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የማታለሎች/Tricks የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ *The Canyon* እና ኮዮቴ በጥንቸሏ በታለለበት ወቅት ምን ስሜት ተሰምቶት ሊሆን እንደሚችል በተመለከተ ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ኮዮቴ በጥንቸሏ በታለለበት ወቅት ምን ስሜት ተሰምቶት ሊሆን እንደሚችል የሚያስበውን እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **ኮዮቴ በጥንቸሏ በታለለበት ወቅት ምን ስሜት ተሰምቶት ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ? ሰው ቢያታልልህ ምን ስሜት ሊሰማህ ይችላል?** ብለው ይጠይቁት።

ስም፡ ______________

ኮዮት በጥንቸል በተታለለ ጊዜ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?



© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ____________________

ኮዮት በጥንቸል በተታለለ ጊዜ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## STEM: ቅርጽ ማደን/መፈለግ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ በሳምን 1 በካርዶች የተቆራረጡ ቅርጾች**



- ለልጅዎ **በቤት ውስጥ ዙሪያ የሚገኙ ቅርጾችን መፈለጋችንን እንቀጥል እና እንደነዚህ አይነት ቅርጾች ያላቸው ነገሮችን ማግኘት የምንችል መሆኑን እንመልከት** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ በቤትዎ ውስጥ የሚገኙትን ቅርጾች መገንዘብና ማነጻጸር እንዲችል ለመርዳት የክብ፣ ስኩዌር፣ ሶስት ማዕዘን እና የዳይመንድ ካርድ ይስጡት።

## በግል መማር: የእኔ አፈ ታሪክ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ማያ ከተባሉት ህዝቦች ስብስብ የተገኘ አፈ ታሪክ የሆነውን*The Canyon*ን እንብበናል። አፈ ታሪክ ሰዎች ደግመው ደጋግመው የሚናገሩት ታሪክ ነው።**
- **የራስህን አፈ ታሪክ መጻፍ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ የራሱን አፈ ታሪክ እራሱን ችሎ እንዲጽፍ እና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **ስለ አፈ ታሪክህ ልትነግረኝ ትችላለህ? ታሪኩን በኋላ አንድ ላይ ሆነን ልንተውነው እንችላለን!** ብለው ይንገሩት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 2 ቀን 8

## ማንበብና መጻፍ፡ ጥንድ ቃላትን መመስረት እችላለሁ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ በክፍሎች የተከፋፈሉ** [ጥንድ ቃላት 3]



- ለልጅዎ **ስለ ጥንድ ቃላት በተመለከተ ተምረናል። እኔ በምሰጥህ ስዕሎች ተጠቅመህ ጥንድ ቃላት መመስረት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ የdoorbell ክፍሎችን ይስጡት። ከዚያም **የdoorbell ስዕልን ፈልግ። door** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **bellን የመሰረቱት ሁለት ቃላት ምንድን ናቸው? በመጀመሪያ door የሚለውን ቃል ስለምሰማ የበር ስዕል እፈልጋለሁ ማለት ነው** ብለው ይንገሩት። ቃሉን ከበር ደውል ስዕሉ በታች ያስቀምጡት።
- **ከዚያም bell የሚለውን ቃል እሰማለሁ** ይበሉት። የደውሉን ስዕለል ከበሩ ስዕል አጠገብ ያስቀምጡት። **Door** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **bell፣ doorbell!** የሚለውን ቃል በሚናገሩበት ወቅት ቃላቱን ጠቁመው ያሳዩት።
- ልጅዎን የfirefly እና sunflower ስዕሎችን እንዲፈልግ ይፍቀዱለት። ሞቅ ያለ ሙገሳ ያድርጉለት፤ **በከፍተኛ ትጋት ሰርተሀል!** ለልጅዎ እርዳታ ቢያደርጉለት ገና በመማር ላይ ስለሆነ ምንም አይደለም!

## ያንብቡ፡ ጥልቅ ዘለቆ/ ***The Canyon***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*ጥልቅ ሸለቆ/The Canyon*]




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *The Canyon* ን ያንብቡ።
- ከዚያም **ኮዮቴ የጮኸው ለምንድን ነው? ኮዮቴ በጥንቸሏ በታለለበት ወቅት ምን ስሜት ተሰምቶት ይሆናል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 2 ቀን 8

## እስኪ እንንቀሳቀስ: እኔን ተከተለኝ

- ለለልጅዎ **እስኪ እኔን ተከተለኝ ጨዋታ እንጫወት። እኔ የምለውን አዳምጥ እና ከዚያም አድርግ!** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ባለ አንድ ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት: ዝለል፣ ጣቶችህን በፍጥነት አንቀሳቅስ፣ በእጆችህ አጨብጭብ፣ ወዘተ
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያዎችን መስጠት እንዲችል ሚናዎቻችሁን ተቀያየሩ።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፡ አፈ ታሪኬን ሆኖ መተወን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ልጅዎ ቀደም ሲል የጻፈው አፈ ታሪክ፣ *በአማራጭነት - እግሮች ወይም አፈ ታሪኩን መስሎ ለመተወን የሚገለግሉ ቁሶች***

- ለልጅዎ **ዛሬ ቀደም ብለህ የጻፍከው አፈ ታሪክ አለ። አሁን አፈ ታሪኩን በጋራ እንተውናለን ወይም እኔ በምተውንበት ወቅት አንተ ታነባለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ በሚያነብበት ወይም አፈ ታሪኩን በሚተውንበት ወቅት እርስዎ ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ እንዲነግርዎ ይፍቀዱለት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




















© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ሰን



ፍላወር



ሰንፍላወር



ሬይን



ኮት



ሬይንኮት


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ጸጉር



ቡርሽ



የጸጉርቡርሽ



ጆሮ



ቀለበት



የጆሮቀለበት


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 2 ቀን 9

## **STEM:** ጥልቅ ሸለቆ መስራት



በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

©2020. AppleTree Institute. All Rights Reserved.

Playdough Recipe (FE)

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ቁሳቁሶች: ካለፈው ሳምንት የተወሰደ ጥልቅ ሸለቆ/Canyon፣ በቀን 7 የተሰራ የጥልቅ ሸለቆ ስዕል፣ የመጫወቻ ሊጥ ወይም በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ**

- ከልጅዎ ጋር በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ስለሰራቸው የጥልቅ ሸለቆ ስዕሎችና የጥልቅ ሸለቆ ቅቦች ይነጋገሩ። ከዚያም **የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም ጥልቅ ሸለቆ መስራት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ጥልቅ ሸለቆዎች ጎንና ጎናቸው የሚያዳልጥ ወይም ከፍ ያለ መሆኑን በማስታወስ እራሱን ችሎ ጥልቅ ሸለቆውን እንዲሰራ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ጥልቅ ሸለቆህ ንገረኝ። ሸለቆውን እና ከፍ ያሉ ጎኖቹን ልታሳየኝ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር: የአካል ምልክት ስም መጥራት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች: **ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመግባባት አካሎቻችንን ወይም ፊታችንን ልንጠቀም እንችላለን። እስኪ የአካል ምልክት ስም መጥራት ጨዋታ እንጫወት። እኔ የአካል ምልክት አሳይህ እና አንተ ምን ማለት እንደሆነ ትነግረኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- ከሚከተሉት መካከል ከ2-3 የአካል ምልክቶች በመጠቀም ጌሙን ተጫወቱ:
  - ራስን ወደ ፊት መነቅነቅ - አዎ
  - ራስን ወደ ጎን መነቅነቅ - አይደለም
  - ጣቶችዎን ከንፈሮችዎ ላይ ማድረግ - ፀጥታ
  - እጅዎን ማወዛወዝ - ሰላምታ መስጠት ወይም መሰናበት
- ከልጅዎ ጋር የተለያዩ የአካል ምልክቶቹን ሊጠቀም ስለሚችልባቸው ጊዜያት ይነጋገሩ። ከዚያም **የሚያነሱትን ምልከት ተጠቅመው እራስዎን ይሳሉ።** ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስላነሳኸው ምልክት ንገረኝ። ይህን ምልክት የምትጠቀመው መቼ ነው?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## ማንበብና መጻፍ: መመሪያዎችን እየተከተልኩኝ ነው?

- ለልጅዎ **እስኪ ጌም እንጫወት። አንተ ለእኔ የምከተለው መመሪያ ልትሰጠኝ ትችላለህ። ከዚያም በትክክል ስለመስራቴ ትነግረኛለህ ወይም ትክክል ካልሆንኩኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ታሳየኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ መመሪያ እንዲሰጥዎት ይፍቀዱለት። ልጅዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ እንዲያሳይዎ ለመፍቀድ መመሪያውን አብዛኛውን ጊዜ ሆን ብለው እየተሳሳቱ አንዳንዴ በትክክል ይከተሉ፤ ምሳ፡ ከማጨብጨብ ይልቅ ይዝለሉ።

## የጆርናል ሙከራ: ኮዮቴ ወይም ጥንቸል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ የኮዮቴ ወይም ጥንቸል የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በ *The Canyon* ውስጥ ስላሉት ኮዮቴና ጥንቸል እና እነሱን መምሰል ምን የመስላል ብለው እንደሚያስቡ በተመለከተ ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ጥንቸል ወይም ኮዮቴን ቢሆን ምን እንደሚያደርግ እራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ምን እንደጻፍክ ንገረኝ። ኮዮቴን ነው ወይስ ጥንቸልን ለመሆን ወሰንክ?** ብለው ይጠይቁት።


ስም: _______________

ጥንቸል ወይም ኮዮቴ መሆን ብትችሉ ምን እንደምታደርጉ ጻፉ እና በስዕል ሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ________________

ጥንቸል ወይም ኮዮቴ መሆን ብትችሉ ምን እንደምታደርጉ ጻፉ እና በስዕል ሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨውን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።






© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 2 ቀን 10

## **STEM:** የመለየት ምርመራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ ማንኪያዎች፣ ኩባያዎች፣ ከለሮች፣ እርሳሶች የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች (የእያንዳንዱ አይነት ቢያንስ 2)**

- ለልጅዎ **እስኪ እነዚህን ነገሮች እንለይና ተመሳሳይ የሆኑትን አንድ ላይ እናስቀምጣቸው። እኔ ሁሉንም ማንኪያዎች አንድ ላይ አደርጋቸዋለሁ** ብለው ይንገሩት።
- **እስኪ ቀሪዎቹን እንለይ** ይበሉት። ልጅዎ ቁሶቹን አንድ ላይ እንዲያስቀምጥ ያድርጉ።
- ቁሶቹን አንድ ላይ ያስቀምጡ እና **ቁሶቹን ለይተን ማስቀመጥ የምንችልበት ሌላ ዘዴ ማሰብ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት። መለየት የሚቻልባቸው ሌሎች ዘዴዎችን ቢጠቁሙም ምንም ማለት አይደለም። ቁሶቹን በመጠናቸው፣ ቅርጻቸው፣ ቀለማቸው ወይም በአገልግሎታቸው፤ ለምሳሌ፡ የምንጽፍባቸው ቁሶች (እርሳስ፣ ከለር) እና ለመብላትና ለመጠጣት የምንጠቀምባቸው ነገሮች (መማንኪያዎች እና ኩባያዎች) መለየት ትችላላችሁ።

## በግል መማር፡ አይሆንም ማለት ጥሩ ሊሆን ይችላል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **መብቶች አሉህ። መብት ማለት ማግኘት ወይም ማድረግ የምትችለው ነገር ነው። ደህንነትህ እንዲጠበቅ የማድረግ እና ምርጫዎች የመምረጥ መብት አለህ** ብለው ይንገሩት።
- **ደህንነት የማይሰማህ ከሆነ ወይም የእድሜ እኩያህ የሆነን ሰው የሆነ ነገር እንድትናገርለት ቢጠይቅህ አይሆንም ማለት ትችላለህ። የማታውቃቸው ሰዎች ከነሱ ጋር የሆነ ቦታ እንሂድ ቢሉህ አይሆንም ማለት አለብህ** ብለው ይንገሩት።
- **አይሆንም ማለት ስለምትችልበት ሌላ ጊዜ ልታስብ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት። ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ እና ከዚያም ልጅዎን እራሱን ችሎ አይሆንም ማለት ስለሚችልባቸው ጊዜያት እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ምን እንደጻፍክ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## ማንበብና መጻፍ: ጥንድ ቃላት



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ቀደም ሲል በዚህ ሳምንት በክፍሎች የተከፋፈሉ** [**ጥንድ ቃላት 3**]

- ለልጅዎ **እስኪ እኔ በምሰጥህ ስዕሎች ተጠቅመን ጥንድ ቃላት እንመስርት** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ የraincoat ክፍሎችን ይስጡት። ከዚያም **የraincoat ስዕልን ፈልግ። rain** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **coatን የመሰረቱት ሁለት ቃላት ምንድን ናቸው? በመጀመሪያ rainን እሰማለሁ። ከዚያም rainን እፈልጋለሁ** ብለው ይንገሩት። ቃሉን ከዝናብ ልብስ ስዕሉ በታች ያስቀምጡ።
- **በመቀጠልም coat እሰማለሁ** ይበሉት። ቃሉን ከዝናብ ስዕሉ ቀጥሎ ከሚገኘው የኮት ስዕል ስር ያስቀምጡት። **Rain** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **coat, raincoat!** ብለው በሚናገሩበት ወቅት ቃላቱን ጠቁመው ያሳዩት።
- ልጅዎን የearring እና hairbrush ፍሎችን እንዲፈልግ ይፍቀዱለት። ሞቅ ያለ ሙገሳ ያድርጉለት፤ **እጅግ በታታሪነት ሰርተሀል!** ልጅዎ ገና በመማር ላይ ስለሆነ እርዳታ ቢያደርጉለትም ምንም ማለት አይደለም!

## ያንብቡ: ጥልቅ ሸለቆ/***The Canyon***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [ጥልቅ ሸለቆ/*The Canyon*]




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *The Canyon* ን ያንብቡ።
- ከዚያም **ጥንቸል ኮዮቴን እንዲከተላት ስላልፈለገች አታላዋለች። የሆነ ሰው የሚያስጨንቅህ ከሆነ ምን ብለህ ልትነግረው ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 3


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ጠቅላላ ምልከታ

## በአለም ዙሪያ የሚገኙ ሁሉም ነገሮች

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ:

የአለም ዙሪያን በመንገድ ጉዞ ስለመጎብኘት፣ በፓስፖርቱን ስለማዘጋጀት እና የሙዚቃ መሳሪያ ስለማዘጋጀት ይማራል። ልጅዎ በተጨማሪም ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት ስለማድረጊያ ተገቢ ዘዴዎች፣ የቃል የድምጽ ቀለሞችነረ ስለመቀላቀል ይማራል እንዲሁም ቅርጾችን መለየት ይለማመዳል።



### ቁልፍ ቃላት



## ባህል

በተወሰነ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የሚጋሩትና ተቀባይነት ያገኘ እምነቶች፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ሥነ ጥበብ/አርት እና ልማዶች ነው።




## ፓስፖርት

በስምዎና ፎቶዎን በመያዝ የሚሰጥዎ ወደ ሌሎች አገራት ለመጓዝ የሚያገለግልዎ ሰነድ ነው።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

አስቡበት!

በዚህ ሳምንት ስለ ጉዞ ትማራላችሁ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት በአካባቢዎ ወይም ከአካባቢዎ ርቀው ስለተጓዙበት ስለሆነ ቦታ ይጻፉ!


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## **STEM:** እስኪ እስከ 7 እንቁጠር

- ለልጅዎ **እስኪ ተራ ድምጾችን በመጠቀም እስከ 7 እንቁጠር። የሮቦት ድምጽ ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ከ 1-2 ተጨማሪ ጊዜያት ይቁሩ። ልጅዎ ድምጾቹን እንዲመርጥ ይፍቀዱለት፤ ምሳ፡ ማንሾካሾክ ወይም አስደንጋጭ ድምጽ።

## በግል መማር፡ የአለምን ስዕል መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [የአለም ካርታ]፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች**




- ለልጅዎ **አለም የተለያዩ አህጉራት ወይም ሰዎች የሚኖሩባቸው የተለያዩ ትላልቅ ቦታዎች አሏት** ብለው ይንገሩት። አህጉራትን ጠቁመው በማሳየት ስማቸውን ይንገሩት እንዲሁም የምትኖሩበትን አህጉር ያሳዩት። **አህጉራት በውሀ የተከበቡ ናቸው። በአብዛኛው ጊዜ በካርታ ላይ መሬት በአረንጓዴ ቀለም እና ውሀ በሰማያዊ ቀለም ይመለከታል። አለምን በየትኛውም የምትፈልገው መልኩ መሳል ወይም መቀባት ትችላለህ!** ብለው ይንገሩት።

- ልጅዎን እራሱን ችሎ የአለም ካርታን እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለቀባኸው አለም ንገረኝ። ለውሀ እና ለመሬት ምን አይነት ቀለሞችን ተጠቀምክ?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## ማንበብና መጻፍ፡ የመቼት ምርመራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** *[በአለም ዙሪያ ያደረግኩት የእግር ጉዞ/My Road Trip Around the World]*




- ልጅዎን **የታሪክ መቼት ምን እንደሆነ ታስታውሳለህ?** ብለው ይጠይቁት። **መቼቶች አንድ ታሪክ የሚካሄድባቸው ቦታዎች ናቸው። መቼቶች ታሪኩን በተሻለ እንድንረዳ ይረዱናል** ብለው ይንገሩት።
- *በአለም ዙሪያ ያደረግኩት የእግር ጉዞ/My Road Trip Around the World* ን ያሳዩት። **ስዕሎች መቼቶችን ያሳዩናል። ይህ ታሪክ ብዙ መቼቶች አሉት! ታሪኩ የተካሄደው በተራሮችና በባህር ዳርቻዎች ላይ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ገጽ 18-19ን ያሳዩት። **እዚህ ላይ ስለሚያዩት መቼት ያብራሩለት። የምታያቸው ሁለቱ መቼቶች ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።

## ያንብቡ፡ *በአለም ዙሪያ ያደረግኩት የእግር ጉዞ/**My Road Trip Around the World***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** *[በአለም ዙሪያ ያደረግኩት የእግር ጉዞ My Road Trip Around the World]*




አለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *በአለም ዙሪያ ያደረግኩት የእግር ጉዞ/ My Road Trip Around the World*ን ያንብቡ።
- ከዚያም በጋራ ሆናችሁ ስለ ባህላችሁ ልዩ ምግቦች ተነጋገሩ። **የምግቦቹ ግብዐቶች ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# የአለም ካርታ





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ቀን 12

## STEM: መስጠም ወይም መንሳፈፍ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ የውሀ መያዣ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ የሚሰጥሙ ቁሶች (ምሳ፡ ሳንቲሞች፣ ማንኪያዎች) እና የሚንሳፈፉ ቁሶች (ምሳ፡ የፕላስቲክ ጠርሙስ ክዳን፣ ከለር)**

- ለልጅዎ **እስኪ እነዚህ ነገሮች ከውሀው ስር ይሰጥሙ ወይም ከላይ ይንሳፈፉ እንደሆነ ለማየት ሙከራ እንስራ። የትኞቹ ይሰጥማሉ እና የትኞቹ ይንሳፈፋሉ ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት። በወረቀት መካከል ላይ መስመር ያስምሩ እና ግምቶቹን በረድፍ 2 "የሚሰጥሙ" እና "የሚንሳፈፉ" ስር ይጻፉ። ከወረቀቱ በታች ውጤቶቹን መጻፊያ ቦታ ይተዉ።
- ልጅዎን የተለያዩ ነገሮች ውሀው ላይ እንዲያስቀምጥ እና ቁሶቹ ይሰጥሙ ወይም ይንሳፈፉ እንደሆነ እንዲያይ ይፍቀዱለት።
- ውጤቶቹን ከታች በትክክለኛው ረድፍ ስር ይጻፉ።
- ከዚያም ውጤቶቹን ከግምቶቻችሁ ጋር ያነጻጽሩ። ቀጥለውም ልጅዎን **ሳንቲሙ ___ ይሆናል ብለን ገምተን ነበር። ግን ተንሳፈፈ ወይስ ሰመጠ? ግምታችን ትክክል ነበር?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር፡ ፓስፖርቴ/የጉዞ ሰነዴ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ፓስፖርት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ፓስፖርትን ወደ ሌሎች አገራት ለመጓዝ ሰዎች ማን እንደሆንን እንዲያውቁ እንጠቀምበታለን። ፓስፖርቱ ፎቷችንን እና የምንጓዝበት የእያንዳንዱን አገር ማህተም ይይዛል** ብለው ይንገሩት።
- **ስዕል በመሳል እና ስምህን እና የትውልድ ቀንህን በመጻፍ የራስህን ፓስፖርት ማዘጋጀት ትችላለህ። መጓዝ የምትፈልግባቸውን ቦታዎች ማህተምም መስራት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ይህን መረጃ በፓስፖርቱ ላይ የትኛው ቦታ ላይ እንደሚያሰፍር ያሳዩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ በፓስፖርትህ ላይ መምታት የምትፈልጋቸውን ቦታዎች ማህተሞች ንገረኝ። ወደ የትኞቹ ቦታዎች ተጉዘሀል?** ብለው ይጠይቁት።
- በተጨማሪም ልጅዎ ስለተለያዩ አገራት የሚረዳና የተለያዩ አገራትን የሚያውቅ ከሆነ ስለምትጎበኟቸው አገራት ቦታዎች ልትነጋገሩ ትችላላችሁ።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## ማንበብና መጻፍ፡ የቃል የድምጽ ቀለሞችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ አንድ ቃል ለመመስረት የሁለት ቃላት የድምጽ ቀለሞችን እንቀላቅል!** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ የአንድ ቃል ሁለት ክፍሎችን እጠራለሁ። አንተ ክፍሎቹን አንድ ላይ አድርገህ ቃሉን ትነግረኛለህ። Din** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **ner። Din-ner። ቃሉ ምንድን ነው? አዎ፤ dinner!** ብለው ይንገሩት።
- በሚከተሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ: mountain (moun-tain) እና summer (sum-mer)። ልጅዎ ቃላቱ ላይ እርዳታ ቢያስፈልገው እንኳ ምንም አይደለም! ገና በመማር ላይ ስለሆነ!

## የጆርናል ሙከራ፡ ቅርጾች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የቅርጾች የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተለያዩ ቅጾች ይነጋገሩ። በአካባቢዎ የሚያዩዋቸውን ቅርጾች ጠቁመው ያሳዩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የሚመርጣቸውን ቅርጾች ተጠቅሞ ስዕል እንዲስል ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ። ምን አይነት ቅርጾችን ተጠቀምክ?** ብለው ይጠይቁት።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ፓስፖርት

ስም:

የትውልድ ቀን:

እዚህ ጋር ማህተም ያድርጉ

እዚህ ጋር ማህተም ያድርጉ

# ፓስፖርት


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ________________

የምትወዷቸውን ቅርጾች በመጠቀም ስዕል ሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ቀን 13

## STEM: ምን ያክል ጣቶች አሉ?

- 2 ጣቶችዎን ወደላይ ያድርጉ እና ልጅዎን **ወደ ላይ ያደረግኩት ምን ያክል ጣቶችን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን ጣቶችዎን ሳይቆጥር መልሱን እንዲናገር ያበረታቱት፣ ሆኖም ለማረጋገጥ ቢቆጥርም ምን አይደለም። ስለ ጥረቱ ያሞግሱት። **ጥሩ ስራ ነው፣ በታታሪነት ሰርተሀል!**
- ከ0 (መጀመሪያ የእርስዎን ያሳዩ) እስከ 3 በሚደርሱ መጠኖች ላይ ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎን ጣቶቹን ሳይቆጥሩ ብዛታቸውን እንዲነግሩት ጣቶቹን እንዲያሳይዎ ይጠይቁት።

## በግል መማር: የመንገድ ገብኝት እቅድ ማዘጋጀት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** **[የአሜሪካ ካርታ]**፣ **ከለሮች**




- ለልጅዎ **ፓትሪክ እና እናቱ በአገራችን በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ዙሪያ የመንገድ ጉብኝት ለማድረግ ሄደዋል። አንተም የመንገድ ጉብኝት ማቀድ ትችላለህ! መሄድ የምትፈልግበትን ቦታ ካርታ ሳል** ብለው ይንገሩት።
- የምትገኙበትን ቦታ በካርታ ላይ ያሳዩት እና በካርታው ላይ የምትገኙበት ቦታ ላይ ምልክት እንዲያደርግ ይርዱት።
- ልጅዎዎ እራሱን ችሎ ካርታ ላይ በመሳል የመንገድ ጉብኝት እቅዱን እንዲያዘጋጅ ያድርጉ። ልጅዎ መስመሩን ለማሳየት መስመር ሊያሰምር እና ማድረግ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ስዕሎች ሊስል ይችላል።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ መንገድ ጉብኝትህ ንገረኝ። መሄድ የምትፈልገው የት ነው? በጉዞህ ላይ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ቀን 13

## ማንበብና መጻፍ: የዋና ገጸ ባህሪ ምርመራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *[በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ/My Road Trip Around the World]*

- **ዋና ገጸ ባህሪ ታሪኩ የሚመለከተው ሰው ነው። ገጸ ባህሪው ሰው ወይም እንስሳ ሊሆን ይችላል** ብለው ይንገሩት።
- *በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞMy Road Trip Around the World* ላይ ስዕሎቾችን ተመልከቱ። ቀደም ብለን ***በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞMy Road Trip Around the World*** ንባብን አንብበናል። **የዚህ መጽሀፍ ዋና ገፀ ባህሪ ማን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን መርዳት ቢኖርብዎትም ምንም ማለት አይደለም። ገና በመማር ላይ ስለሆነ! **አዎ፡ ታሪኩ ፓትሪክን የተመለከተ ነው** ብለው ይንገሩት።
- **ስለ ፓትሪክ ልትገልጽልኝ ትችላለህ? ስለ ፓትሪክ ምን ታስታውሳለህ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን ገጸ ባህሪውን እንዲያስታውስ ለመርዳት ፈጣን የስዕል ምልከታ ልታደርጉ ትችላላችሁ። ልጅዎን **እንደ ፓትሪክ የፊት ጥርስ የሌለው ልጅ ነው** ወይም **ፓትሪክ በዙ የተለያዩ ምግቦችን መሞከር ይፈልጋል** አይነት ዝርዝሮችን በመስጠት ይርዱት።

## ያንብቡ: *በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *[በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ/My Road Trip Around the World]*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ/My Road Trip Around the World*ን ያንብቡ።
- ከዚያም ከልጅዎ ጋር ፓትሪክ ስለተመገበው ምግብ እና የትኞቹን ምግቦች መሞከር እንደሚፈልግ በተመለከተ ይነጋገሩ። ከዚያም **ፓትሪክ ከተመገባቸው ምግቦች ውስጥ የትኞቹን መሞከር ትፈልጋለህ? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።



አለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ቀን 13

## እስኪ እንንቀሳቀስ: እስከ 7 መቁጠር እና ማቆሚያ መምታት!

- ለልጅዎ **እስኪ እየደነስን እስከ 7 እንቁጠር። 7 ላይ ስንደርስ እናቁምና ተራ ማቆሚያ እንስራ! አቁመን እንደ ኮዮቴ ግድግዳ መያዝ አስመስለን ልንሰራ ወይም በምትፈልገው መልኩ ልንቆም እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- **ተዘጋጀህ? እስኪ አንድ ላይ 1, 2, 3, 4, 5, 6, 7 እንቁጠርና እናቁም!** ብለው ይንገሩት።
- ከ1-2 ተጨማሪ ጊዜያት ቁጠሩና አቁሙ። ልጅዎንም እንዲቆጥር ያበረታቱት!

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፡ የምግብ ዝግጅታችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ እርሳስ ወይም ከለሮች፣ የምግብ ምርጫችሁ ግብአቶች**

- ልጅዎን **ምግብ በባህሎች ውስጥ አስፈላጊ ነው። በባህላችን ከምንመገባቸው ምግቦች መካከል ጥቂቶቹ ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።
- **እስኪ መመገብ የምንፈልገውን ልዩ ምግብ እናንሳና ስለ ምግቡ አዘገጃጀት እንጻፍ** ብለው ይንገሩት። አንድ ምግብ አንሱና ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ምግቡ ይጻፉ። ልጅዎ በመጻፉና ስዕሎች በመሳል ላይ ሊረዳዎ ይችላል።
- አሁን ወይም ቆይታችሁ በጋራ ምግብ አዘጋጁ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ቀን 14

## **STEM:** የማዳመጥ ሙከራዎች

- ለልጅዎ **ለሌሎች ሰዎች በሚናገሩበት ወቅት በማዳመጥ ክብር መስጨጠታችንን እናሳያለን። ማዳመጥና መረዳትን ምን ቀላል እንደሚያደርገው ለማየት እስኪ ጥቂት የማዳመጥ ሙከራዎች እንስራ** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ላይ በተለያዩ የድምጽ መጠኖች ለመነጋገር ሞክሩና ከዚያም የትኛው ለመረዳት እንደሚቀል አነጻጽሩ። የሹክሹክታ ድምጽ፣ መደበኛ የውስጥ ድምጽ እና የጩኸት ድምጽ ተጠቀሙ። ከዚያም ልጅዎን **በመትጮህበት ወቅት ጉሮሮህን ምን አይነት ስሜት ተሰማህ?** ብለው ይጠይቁት።
- እርስ በርሳችሁ እየተያያችሁ እና ወደ ሌላ ቦታ እያያችሁ በሹክሹክታ ድምጽ ለማውራት ሞክሩ። ከዚያም **በሹክሹክታ ስንነጋገር ለመስማት የሚቀለው እየተያየን ስናወራ ነው ወይስ ወደ ሌላ ቦታ እያየን ስናወራ?** ብለው ይጠይቁት።
- በመቀጠልም **በምርምራችን ላይ እንዳየነው በምንነጋገርበት ወቅት የውስጥ ድምጽ መጠቀምና እርስ በርሳችን እየተያየን ማውራት ተመራጭ ነው።**

## በግል መማር: የተመራጭ ቀለም መጽሀፍ ክፍል 1




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** **[የአለም ካርታ ቁርጥራጭ፣]** **ከለሮች ወይም መቀቢያ፣** ***በአማራጭነት - ቁርጥራጮችን ተቆርጠው ከመውጣታቸው በፊት ካርቶን ላይ ማጣበቂያ (ምሳ፡ የጥራጥሬ ሳጥን)***

- ከልጅዎ ጋር ስለ ካርታዎች ይነጋገሩ። **ካርታ አህጉራትን የያዘ የአለም ስዕል ሲሆን አህጉራት በውሀ የተከበቡ ትላልቅ የመሬት አካሎች ናቸው** ብለው ይንገሩት። ከዚያም **የአለም ካርታ ቁርጥራጭ መስራት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ቁርጥራጭ የመገጣጠም ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉት። ልጅዎ በተጨማሪም ቁርጥረራጮቹን ከገጣጠመ በኋላ ሊቀባ ወይም በቀለም ሊያደምቅ ይችላል።
- ከዚያም ለስራ ትጋቱ ያሞግሱት እና **ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ለመገጣጠም በትጋት ሰርተሀል! የምንኖርበትን አህጉር ጠቁመህ ልታሳየኝ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው ጠቁመው ስሙን ይንገሩት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## ማንበብና መጻፍ፡ እስኪ ስለ ባህል እንነጋገር

- ልጅዎን **የተለዩ ባህሎች ላላቸው ሰዎች ክብር መስጠታችንን ወይም ትህትናችንን እንዴት ማሳየት እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት። ድጋፍ የሚያስፈልገው ከሆነ እንደ እባክዎና አመሰግናለሁ የመሳሰሉ ምሳሌዎች፣ ስለ እነዚህ ሰዎች ባህሎች ለማወቅ ከፈለግን የእኛን የማካፈልና ጥያቄዎች የመጠየቅ ምሳሌዎች ይስጡት።
- ልጅዎን ከ2-3 የክትትል ጥያቄዎች ይጠይቁት፤ ለምሳሌ **ይህን ለምን አሰብክ?** ወይም **ለሌላ ሰው ትሁት ስለነበርክበት ጊዜ ልትነግረኝ ትችላለህ**? የምልልስ ውይይቶች ልምምድ ያድርጉ።
- ልጅዎ ስለ ባህል መነጋገር የማይፈልግ ከሆነ ልጅዎን በዚህ ምትክ ስለ ምን መነጋገር እንደሚፈልግ ሊጠይቁት ይችላሉ።

## የጆርናል ሙከራ፡ አዲስ ምግብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የአዲስ ምግብ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው መሞከር ስለሚፈልጋቸው ስለተለያዩ የምግብ አይነቶች ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ መሞከር ስለሚፈልገው የምግብ አይነት እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ መሞከር ስለምትፈልገው ምግብ ንገረኝ። ይህን የምግብ አይነት ለምን መረጥከው?** ብለው ይጠይቁት።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ________________

ምን ዓይነት ምግብ መሞከር ትፈልጋላችሁ?


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## STEM: ምን ያክል ቁሶች አሉ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ ከለሮች ወይም ማንኪያዎች የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች፣ የእያንዳንዳቸው 3 ብዛት**

- ለልጅዎ ሶስት ከለሮች ያሳዩት እና **ምን ያክል ከለሮች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን ከለሮቹን ሳይቆጥር እንዲመልስ ያበረታቱት፣ ሆኖም ለማረጋገጥ ቢቆጥራቸውም ምንም አይደለም። ስለ ጥረቶቹ ያሞግሱት፤ **ጥሩ ስራ ነው፤ በታታሪነት ሰርተሀል!**
- ከ0 እስከ 3 ባሉ መጠኖች ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግመው ይስሩ። ለልጅዎ እርስዎ ቁሶቹን መጠናቸውን ሳይቆጥሩ እንዲነግሩት ቁሶቹን እንዲያሳይዎ ይፍቀዱለት።

## በግል መማር: የራንጎሊ ዲዛይኖች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [የራንጎሊ ዲዛይኖች/Rangoli Designs]፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች**

- ለልጅዎ **አርት በባህሎች ውስጥ አስፈላጊ ነው። ራንጎሊ ህንድ ውስጥ ወለል ላይ የደረቀ ሩዝና አሸዋ ወይም የአበባ ዱቄቶች በመጠቀም ፓተርኖች የሚስሉበት አርት ነው። ህንዳውያን ራንጎሊን በወሳኝ ክብረ በአላቸው ዲዋሊ ወቅት ይጠቀሙበታል። የራስህን የራንጎሊ ዲዛይን ልትቀባ ትችላለህ!** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ዲዛይኖቹን እንዲቀባ ይፍቀዱለት። ልጅዎ በተጨማሪም የራሱን ዲዛይን ሊስልና ሊቀባ ይችላል።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ዲዛይንህ ንገረኝ። እነዚህን ቀለሞች ለምን መረጥካቸው?** ብለው ይጠይቁት።




© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 3 ቀን 15

## ማንበብና መጻፍ፡ ባለ ሶስት የድምጽ ቀለም ቃላትን መቀላቀል

- **ዛሬ ባለሶስት ምት ወይም የድምጽ ቀለም ቃላትን ስለመቀላቀል እንማራለን። ምቶቹን ከእኔ ጋር አብረህ ቁጠር፡ con-struc-tion። ምን ቃል ትሰማለህ? Construction!** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እስኪ የድምጽ ቀለሞችን እንቀላቅል!** ይበሉት።
- **እኔ የአንድን ቃል ክፍሎች እጠራለሁ። አንተ ክፍሎቹን አንድ ላይ አገናኝተህ ቃሉን ትነግረኛለህ። Blue** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **ber** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **ry። Blue-ber-ry። ቃሉ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ለልጅዎ ሞቅ ያለ ሙገሳ መስጠትን አይርሱ! **ጥሩ ስራ ነው!**
- በሚከተሉት ቃላት ደግመው ይስሩ: rectangle (rec-tan-gle) እና character (char-ac-ter)።
- ልጅዎ በዚህ ላይ ተጨማሪ ልምምድ ቢፈልግ ምንም አይደለም።

## ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ: በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***አለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ/My Road Trip Around the World***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *በአለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ/ My Road Trip Around the World*ን ያንብቡ።
- ከዚያም **የዚህ ታሪክ ዋና ዋና ገጸ ባህሪያት እነማን ናቸው?** (ፓትሪክና እና እናቱ)። **ከታሪኩ መቼቶች መካከል አንደኛው የት ነው? የአንተ ተመራጭ መቼት የትኛው ነው?** ብለው ይጠይቁት።



አለም ዙሪያ የማደርገው የመንገድ ጉዞ


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 4


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ጠቅላላ ምልከታ

## የባህል ምርመራ

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ:

የራሱን ባህል ጨምሮ ስለተለያዩ ባህሎች መማሩን ይቀጥላል። ልጅዎ በተጨማሪም ጥንድ ቃላት መመስረትን፣ የድምጽ ቀለሞች መቀላቀልን እና እስከ 7 መቁጠርን ይለማመዳል።



### ቁልፍ ቃላት



## አልባሳት

የምንለብሳቸው ነገሮች ናቸው፤ ለምሳሌ: ሸሚዞችና ሙሉ ልብሶች



## የተሸመነ ልብስ

በአሻንቲ ሰዎች ተሸምኖ የሚሰራ ልብስ ነው



© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

**አስቡበት!**

ይህ ባህልን የተመለከተው ክፍል የመጨረሻ ሳምንታችን ነው። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት እስካሁን ከተማራችሁት ትምህርት ውስጥ ስለወደዱት ነገር ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ቀን 16

## STEM: መቁጠር እና መንቀሳቀስ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እየሰራችሁ እስከ 7 መቁጠር ተለማመዱ። ከዚያም **እስኪ እስከ 7 እየቆጠርን በተለያዩ ዘዴዎች እንቅስቃሴ እናድርግ! በመንገድ ጉዞ ላይ እንደምናሽከረክር እያስመሰልን እሰከ 7 መቁጠር እንችላለን። 1, 2, ...7! ጥሩ መነሳሳት ነው!** ይበሉት።
- ሹካ፣ ወዘተ በመጠቀም እንደ የጓሮ አትክልት መትከል የመሳሰሉ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ስሩ። ልጅዎም እንቅስቃሴዎችን እንዲጠቁም ይፍቀዱለት።

## በግል መማር: የተሸመነ ልብስ መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች፣ ወረቀት (2 ሉኮች)፣, [የተሸመነ ልብስ]()**



- ለልጅዎ **አልባሳት በባህሎች ውስጥ አስፈላጊ ናቸው። አልባሳት ከጨርቅ ይሰራሉ። የተሸመነ ልብስ በአሻንቲ ባህል ውስጥ አስፈላጊ ነው። የአሻንቲ ህዝብ አፍሪካ አህጉር ውስጥ በምትገኘው በጋና አገር ውስጥ ይገኛሉ። የአሻንቲ ህዝቦች ቀጫጭን የልብስ ክሮችን በማዘጋጀት በሽመና ልብስ ይሰራሉ** ብለው ይንገሩት። የተሸመነ ልብስ ምሳሌ ያሳዩት።
- **ይህን ወረቀት ልብስ አስመስለን እንሰራለን። የልብስ ስዕል መስራት/መቀባት እና ዲዛይን ማዘጋጀት ትችላለህ። እነዚህን በሌላ ቀን አንድ ላይ ትሰፋቸዋለህ** ይበሉት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ወረቀቱን እንዲቀባ ያድርጉ። ልጅዎ በ2 ወረቀቶች ላይ በዚህ ሳምንት መጨረሻ ላይ አንድ ላይ የሚሰፋቸው ዲዛይኖች መሳል/መቀባት አለበት።

- ቀጥለውም **እስኪ ስለሰራኸው ዲዛይን ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት። የተቀባውን ወረቀት በቀን 17 ለሚሰራው ተግባር ያስቀምጡት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## ማንበብና መጻፍ: ጥንድ ቃላት



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: በክፍሎች የተከፋፈሉ** **ጥንድ ቃላት 4**

- ለልጅዎ **በምሰጥህ ስዕሎች ተጠቅመህ ጥንድ ቃላትን ትመሰርታለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ የrattlesnake ክፍሎችን ይስጡት። ከዚያም **የrattlesnakeን ስዕል ፈልግ። rattle** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **snakeን የመሰረቱት ሁለት ቃላት ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።
- **በመጀመሪያ የምትሰማው ቃል ምንድን ነው? አዎ rattle ነው፣ ስለዚህ rattleን እፈልጋለሁ** ይበሉት። ቃሉን ከrattlesnake በታች ያስቀምጡ። **ቀጥዬ snakeን እሰማለሁ።** የእባቡን ስዕል ከrattle ስዕል ጎን ያስቀምጡት። **Rattle** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **snake፣ rattlesnake!** ብለው እየተናገሩ ቃላቱን ጠቁመው ያሳዩት።
- ለልጅዎ የstarfish እና rainbow ክፍሎችን እንዲፈልግ ይፍቀዱለት። ከፍ ያለ ሙገሳ ያድርጉለት፤ **በጣም በታታሪነት ሰርተሀል!** ለልጅዎ እርዳታ ቢያደርገለትም ምንም አይደለም። ገና እየተማረ ስለሆነ!
- ቀሪ የተግባር ክፍሎችን ለሳምንቱ መጨረሻ ተግባር ያስቀምጧቸው።

## ያንብቡ: የሶፊ የአትክልት ቦታ/***Sophie's Garden***




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***የሶፊ የአትክልት ቦታ/Sophie's Garden***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የሶፊ የአትክልት ቦታ/Sophie's Garden*ን ያንብቡ። ከገጽ 2-19 ያሉትን እያንዳንዱን የፍራፍሬ ስዕሎች በመንካት ይቁጠሩ።
- ከዚያም ገጽ 9ን ያሳዩት እና **ምን ያክል ስትሮበሪዎች ይታዩሀል?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ፍራፍሬዎቹን በማየት ከመንገር ይልቅ መቁጠር ቢያስፈልገውም ምንም አይደለም።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

**የተሸመነ ልብስ FE)**


ራትል


ስኔክ


ራትል ስኔክ


ስታር


ፊሽ


ስታርፊሽ


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ሬይን



ቦው



ሬይንቦው



አርም



ቼር



አርምቼር


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።









© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ቀን 17

## STEM: ከተማችንን መገንባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ብሎኬቶች ወይም እንደ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ጠርሙሶችና የእቃ መያዣዎች፣ የወረቀት ጥቅሎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **ፓትሪክና እናቱ በመንገድ ጉዟቸው ላይ የተለያዩ ቦታዎችን አይተዋል። እስኪ እነዚህን ብሎኬቶች አንድ ላይ ከተማችንን ለመገንባት እንጠቀምባቸው** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር ሆነው በከተማችሁ ውስጥ ስለሚገኙ ከልጅዎ ጋር ሆነው በብሎኬት መገንባት ስለምትችሏቸው አንዳንድ ልዩ ህንጻዎችና አቀማመጦች ይነጋገሩ።

## በግል መማር: የተሸመኑ ልብሶች በሽመና መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከቀን 16 የተወሰዱ የተሸመኑ ልብሶች ዲዛይኖች፣ ለህጻናት ደህንነት ተስማሚ መቀሶች**



- ቀለም ከተቀቡት ገጾች መካከል አንደኛውን ግማሽ ላይ ይጠፉ። ማጠፍ ሲጀምሩ እኩል ቦታ የተቆራረጡ ቁራጮች ያውጡ። ከወረቀቱ ጫፍ (ተቃራኒ ጠርዝ) ½ ጠርዝ ላይ ሲደርሱ መቁረጥ ያቁሙ።
- ለልጅዎ **የተሸመነ ልብስ መስራትህን በዚህ ወረቀት ውስጥና ውጭ በሽመና በመስራት ማጠናቀቅ ትችላለህ። በመጀመሪያ የተሸመነ ልብስህን ቀጫጭን ክሮች ቆርጠህ እንድታወጣ እረዳሀለሁ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ የሸና ስራውን እንዲያጠናቅቅ ለማስቻል የተሸመኑ ቀጫጭን ክሮችን እንዴት በወረቀቱ ውስጥና ከውጭ እንደሚሰፋ ምሳሌ ይስጡት።
- ከዚያም **እስኪ የሽመና ልብስ መስራት ምን አይነት ስሜት እንደሚፈጥር ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ቀን 17

## ማንበብና መጻፍ፡ ባለ ሶስት የድምጽ ቀለም ቃላትን የመቀላቀል ምርመራ

- ለልጅዎ **እስኪ አንድ ቃል ለመመስረት ባለ ሶስት የድምጽ ቀለም ቃላትን አንድ ላይ እንቀላቅል!** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ የአንድ ቃል ሶስት ክፍሎችን እጠራለሁ። አንተ ደግሞ ክፍሎቹን አንድ ላይ አድርገህ ቃሉን ትነግረኛለህ። An** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **i** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **mal። An-i-mal። ምን ቃል ይሰማሀል? Animal!** ይበሉት።
- በሚከተሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ: ambulance (am-bu-lance) እና strawberry (straw-ber-ry)። ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው ሊረዱት ይችላሉ። ገና እየተማረ ስለሆነ!

## የጆርናል ሙከራ፡ የአትክልት ቦታዬ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የአትክልት ቦታዬ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ልጅዎ ልክ እንደ የሶፊ የአትክልት ቦታ ቢኖረው መትከል ስለሚችላቸው ስለተለያዩ ነገሮች ተነጋገሩ።
- ልጅዎን በአትክልት ቦታው ምን እንደሚተክል እራሱን ችሎ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ የአትክልት ቦታ ቢኖርህ ምን እንደምትተክል ንገረኝ። እነዚህን ነገሮች ለምን መረጥካቸው?** ብለው ይጠይቁት።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: _________________

የአትክልት ቦታ ቢኖራችሁ ምን ታበቅላላችሁ?


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ቀን 18

## **STEM:** የምን ያክል ምርመራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ ከለሮች ወይም ማንኪያዎች ያሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፣ የእያንዳንዱ አይነት 3**

- 2 ከለሮች ያሳዩት እና **ምን ያክል ከለሮች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን ከለሮቹን ሳይቆጥር እንዲመልስ ያበረታቱት፣ ሆኖም ለማረጋገጥ ቢቆጥራቸውም ምንም አይደለም። ስለ ጥረቶቹ ያሞግሱት፤ **ጥሩ ስራ ነው፤ በታታሪነት ሰርተሀል!**
- ከ0 እስከ 3 ባሉ መጠኖች ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግመው ይስሩ። ለልጅዎ እርስዎ ቁሶቹን መጠናቸውን ሳይቆጥሩ እንዲነግሩት ቁሶቹን እንዲያሳይዎ ይፍቀዱለት።

## በግል መማር፡ የጓሮዬን ዲዛይን ማዘጋጀት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የሶፊ *የአትክልት ቦታ/Sophie's Garden***



በሚያምረው የሶፊ የአትክልት ቦታዎች ውስጥ የሚበቅሉትን እስኪ እንቁጠራቸው።

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የሶፊ የአትክልት ቦታ/Sophie's Garden* ከገጽ2-3 ይመልከቱ። በጓሮው ውስጥ ስላያችኋቸው ስለተለያዩ ነገሮች ተነጋገሩ።
- ከዚያም **ዛሬ የራስህን ጓሮ ዲዛይን ማዘጋጀትና መሳል ትችላለህ እንዲሁም ነገ ጓሮውን በመጫወቻ ሊጥ ተጠቅመህ መስራት ትችላለህ** ይበሉት።
- ለልጅዎ እራሱን ችሎ የጓሮውን ዲዛይን እንዲያዘጋጅ ይፍቀዱለት።

- ከዚያም **የጓሮህን ዲዛይን ያዘጋጀኸው እንዴት ነው? ምን አይነት ፍራፍሬዎችና አትክልት ትተክላለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ዲዛይኑን ነገ ጓሮ ስትሰሩ ለመጠቀም ያስቀምጡት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## ማንበብና መጻፍ፡ የጥንድ ቃላት ምርመራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ በክፍሎች የተከፋፈሉ [ጥምር ቃላት 4]**



- ለልጅዎ **በምሰጥህ ስዕሎች ተጠቅመህ ጥንድ ቃላትን ትመሰርታለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ የ armchair ክፍሎችን ይስጡት። ከዚያም **የ armchair ን ስዕል ፈልግ። arm** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **chair ን የመሰረቱት ሁለት ቃላት ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።
- **በመጀመሪያ የምትሰማው ቃል ምንድን ነው? አዎ arm ነው፣ ስለዚህ arm ን እፈልጋለሁ** ይበሉት። ቃሉን ከ armchair በታች ያስቀምጡ። **ቀጥሎ በ armchair ውስጥ የምትሰማው ቃል ምንድን ነው? አዎ chair** ነው። **Arm** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **chair፣ armchair!** ብለው እየተናገሩ ቃላቱን ጠቁመው ያሳዩት።
- ለልጅዎ የ wheelchair እና basketball ክፍሎችን እንዲፈልግ ይፍቀዱለት። ከፍ ያለ ሙገሳ ያድርጉለት፤ **በጣም በታታሪነት ሰርተሀል!** ለልጅዎ እርዳታ ቢያደርገለትም ምንም አይደለም። ገና እየተማረ ስለሆነ!

## ያንብቡ፡ የሶፊ የአትክልት ቦታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*የሶፊ የአትክልት ቦታ/Sophie's Garden*]




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የሶፊ የአትክልት ቦታ/ Sophie's Garden*ን ያንብቡ።
- ከዚያም ገጽ 14-15ን ያሳዩት እና **እስኪ ብሉቤሪዎቹን ቁጠራቸው** ብለው ይንገሩት። ቀጥለውም **ምን ያክል ብሉቤሪዎች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ድምሩን ከመንገር ይልቅ በድጋሚ የሚቆጥር ከሆነ **በጠቅላላው 5 ብሉቤሪዎች አሉ** ብለው ሊነግሩት ይችላሉ። ይህ ልጅዎን መጨረሻ የሚቆጥረው ቁጥር ድምሩ እንደሆነ ለመረዳት ይረዳዋል።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ: እስከ 7 መደነስ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** ***በአማራጭነት - ሙዚቃ***

- ለልጅዎ **እስኪ እየደነስን እስከ 7 እንቁጠር። ምን አይነት የዳንስ እንቅስቃሴ ልታስተምረኝ ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- በእያንዳንዱ ጊዜያት ልጅዎን የዳንስ እንቅስቃሴ አይነቱን እንዲናገር እድል በመስጠት ከ2-3 ጊዜያት አብራችሁ እየደነሳችሁ እስከ 7 ቁጠሩ።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፡ የፋሽን ትዕይንት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ለእርስዎና ለልጅዎ የባህላችሁ ልዩ አልባሳት እና የምትወዳቸው ልብሶች**

- ለልጅዎ **የባህል አንዱ ክፍል አለባበስ ነው። አልባሳት እንደ ኮፍያዎችና ሸሚዞች ያሉ የምንለብሳቸው ልብሶች ናቸው። እስኪ የፋሽን ትእይንት እናካሂድ እና ለባህላችን ልዩ የሆኑ አልባሳትን እንልበስ** ብለው ይንገሩት።
- ልዩ ወይም የሚወዱትን ልብስ ሊመርጡ እና ለልጅዎ አለባበሱ ለእርስዎ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ሊነግሩት ይችላሉ። በተጨማሪም የተለያዩ አይነት አልባሳትን ከስልክ ወይም ታብሌት ላይ መመልከት ትችላላችሁ፤ ለምሳሌ፡ ብሔራዊ አለባበስ፣ የሀገር ሰንደቅ አላማ ቀለሞች የተቀቡ ልብሶች፣ ወዘተ።
- ከልጅዎ ጋር ለምን ይህ ልብስ ልዩ እነደሆነ ይነጋገሩ።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## STEM: ውሀ ውስጥ ጨውና ዘይት መጨመር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ጨው፣ ዘይት (የአትክልት፣ የወይራ ወይም የህጻናት ዘይት)፣ 2 ኩባያ ውሀ**

- 2 ባዶ ኩባያዎችን 2/3ኛ መጠን ይሙሉ። ኩባያዎቹ በውስጥ ምን እንደሚፈጠር ለማየት እንዲችሉ ስስ መሆን አለባቸው።
- ለልጅዎ **እስኪ ውሀው ውስጥ ዘይትና ውሀ ስንጨምር ምን እንደሚፈጠር እንይ። ዘይት ስንጨምር ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ጨው ስንጨምር ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ዘይትና ጨዉ ይሰምጣሉ ወይስ ይንሳፈፋሉ ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ለልጅዎ በአንደኛው ውሀ የያዘ ኩባያ ውስጥ ጥቂት ዘይት እንዲጨምር እና ምን እንደሚታየው (ዘይቱ ከላይ ሲንሳፈፍ) እንዲያብራራ ይፍቀዱለት። በሌላኛው ኩባያ ውሀ ጨውን ጨምረው ይስሩ (ጨዉ በውሀ ውስጥ መስጠም ወይም መሟሟት አለበት)።
- ውጤቶቹን ምን እንደሚፈጠር ከገመታችሁት ጋር አነጻጽሩ።

## በግል መማር: በመጫወቻ ሊጥ የአትክልት ቦታ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከቀን 18 የተወሰደ የልጅዎ የጓሮ ዲዛይን፣ የመጫወቻ ሊጥ ወይም [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ]**

- ለልጅዎ **ትናንትና የአትክልት ቦታ ዲዛይን አዘጋጅተሀል ወይም ስለሀል። ዛሬ ደግሞ ጓሮውን የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም መስራት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን በቀዳሚው ቀን የሰራውን ዲዛይን በመጠቀም እራሱን ችሎ የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም የአትክልት ቦታውን እንዲሰራ ያድርጉ።
- ከዚያም **ስለ አትክልት ቦታህ ልትነግረኝ ትችላለህ? በጓሮህ ውስጥ ምን ነገሮችን አስገባህ? በአትክልት ቦታህ ውስጥ አትክልትና ፍራፍሬዎች አሉ?** ብለው ይጠይቁት።


በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

Playdough Recipe (FE)


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ቀን 19

## ማንበብና መጻፍ፡ እስኪ እንቀላቅል

- ለልጅዎ **እስኪ አንድ ቃል ለመፍጠር ባለ ሁለት እና ባለ ሶስት የድምጽ ቀለሞችን እንቀላቅል!** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ የቃላቱን ሁለት ወይም ሶስት ክፍሎች እነግርሀለሁ። አንተ ደግሞ ክፍሎቹን አንድ ላይ አድርገህ ቃሉን ትነግረኛለህ። Door** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **way። Door-way። ቃሉ ምንድን ነው? አዎ፣ doorway ነው** ብለው ይንገሩት።
- በሚከተሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ: window (win-dow) እና frustrated (frus-trat-ed)። ልጅዎ ድጋፍ ቢያስፈልገውም ምንም ማለት አይደለም። ገና እየተማረ ስለሆነ!

## የጆርናል ሙከራ፡ ባህሌ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች ከለሮች፣ የባህሌ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ባህላችሁ እና ባህላችሁን ምን ልዩ እንደሚያደርገው ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ከባህላችሁ ስለሚወደው ነገር እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ከባህላችን ስለምትወደው ነገር ንገረኝ። ይህን ክፍል የመረጥከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት። እርስዎም ከባህላችሁ ስለሚወዱት ነገር ሊገልጹለት ይችላሉ።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም: ________________

ስለ ባህላችሁ የምትወዱት ክፍል ምንድን ነው?


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 5 ሳምንት 4 ቀን 20

## STEM: ቀናችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **እስኪ ዛሬ ለምናደርገው ነገር የጊዜ ሰሌዳ ወይም ዝርዝር እናዘጋጅ። መርሀግብራችንን በምናዘጋጅበት ወቅት በቅደም ተከተል የምንሰራውን ነገር እንጽፋለን። ስዕሎች መሳልም እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **መጀመሪያ የምናደርገው ምንድን ነው? አዎ _____ እናደርጋለን** (ምሳ፡ ከእንቅልፍ መነሳት፣ ቁርስ መብላት፣ ወዘተ) **በመቀጠል የምናደርገው ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን የሚያደርጋቸውን ቢያንስ ከ2-3 ነገሮች በቅደም ተከተል እንዲናገርና እንዲስል ያድርጉ፤ ለምሳሌ: ከእንቅልፍ መነሳት፣ ቁርስ መብላት፣ የሚያዝናና ነገር ማማመጥ።
- ከዚያም **በመርሀግብራችን ላይ መጨረሻ ያደረግነው ነገር ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር: የባህል ስንብት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **እስከ አሁን ድረስ ስለተለያዩ ባህሎች እና እንዴት ከልዩነታችን ይልቅ በአብዛኛው ተመሳሳይ መሆናችንን ስንማር ቆይተናል** ብለው ይንገሩት። ልጅዎ ጋር ከባህል ውስጥ ስለሚወደው ነገር ይነጋገሩ። ይህ ተመራጭ ተግባር ወየም መጽሀፍ ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ከባህል ውስጥ ስለሚወደው ነገር እንዲስልና እንዲጽ ያድርጉ።
- ከዚያም **ከባህል የምትወደው ነገር ምንድን ነው? ይህን ለምን ልትወደው ቻልክ?** ብለው ይጠይቁት።


© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## ማንበብና መጻፍ፡ እስኪ ስለዚህ ንገረኝ

- ልጅዎን **ከባህላችን ውስጥ እጅግ አስፈላጊው ክፍል ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ከ2-3 የክትትል ጥያቄዎች ይጠይቁት፤ ለምሳሌ **ይህ ምንድነው ብለህ ታስበለህ?** ወይም **ስለ ባህላችን ይህ ክፍል በተጨማሪ ማወቅ የምትፈልገው የትኛውም ነገር አለ?** የምልልስ ውይይቶች ተለማመዱ።
- ልጅዎ ስለ ባህል ማውራት የማይፈልግ ከሆነ ልጅዎን ከዚህ ይልቅ ስለ ምን ጉዳይ ማውራት እንደሚፈልግ ሊጠይቁት ይችላሉ።

## ያንብቡ፡ የሶፊ የአትክልት ቦታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [***የሶፊ የአትክልት ቦታ/Sophie's Garden***]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የሶፊ የአትክልት ቦታ/ Sophie's Garden*ን ያንብቡ።
- ከዚያም **ታሪኩ የተካሄደበት ቦታ የት ነው? መቼቱ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።





© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ወደ ክፍል 5 እንኳን በደህና መጡ! በክፍል 5 ስር ልጅዎ ስለ ባህል ይማራል። ምንም እንኳን ባህሎች አንድ አይነት ባይሆኑም ሙሉ በሙሉ የተለየያዩ ግን አይደሉም። ልጅዎ ስለ ባህል 5 ባህሪያት፡ ምግብ፣ ቋንቋ፣ ክብረ በአላት፣ አለባበስ እና ስነ ጥበብ/አርት ይማራል።



AppleTree
© 2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።